በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡- 202486

ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ አዲሱ ዓለሙ- አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ መስከረም ንጉሴ- ጠበቃ ዳጨው ዳመና- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር መዝገቡ የቀረበው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የአመልካች ሚኒባስ መኪና በሆነ ተሳፍረን በምንጓዝበት ጊዜ ከቆመ ተሽከርካሪ ጋር በመጋጨቱ በቀኝ እግሬ የታፋ አጥንት እና በግራ እግሬ ከጉልበት በታች አጥንት ስብራት በመድረሱ 28% ቋሚ አካል ጉዳት ደርሶብኛል፡፡ የጉዳት ካሣ ብር 406,230.00፣ የሕክምና ወጪ ብር 90,770.00፣ የአልሚ ምግብ ወጪ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 በድምሩ ብር 500,00.00 አመልካች እንዲከፍሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የሠጡት መልስ በንግድ ሕጉ መሠረት በውል ስትጓዝ ነው ጉዳቱ የደረሰው፣ የቀረበው የጉዳት

መጠን የተጋነነ የሚል ሲሆን ለመኪናው የመድን ሽፋን የሠጠው መድን ድርጅት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የጉዳት ካሣ ብር 350,844.00፣ የሕክምና ወጪ ብር 90,770.00፣ የምግብ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 አመልካች እንዲከፍል እና የመድን ሽፋን የሠጠው ድርጅት ብር 40,000.00 እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በመዝገብ ቁጥር 180599 የተሰጠው ውሳኔ ጉዳቱ የደረሰው ተጠሪ ተሳፍረው በሚጓዙበት ጊዜ ስለሆነ በንግድ ሕግ ሊገዛ ይገባል፤ የአመልካች ኃላፊነት የሚወድቀው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 597(1) ስር ነው ወይስ በአንቀጽ 599 የሚለውንና የጉዳት ካሣውን በርትዕ እንዲወስን ጉዳዩን ለሥር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ ጉዳቱ የደረሰው በአንገፍ ጥፋቱ ነው ወይስ አይደለም ለሚለው ጭብጥ ግራቀኙ ማስረጃ መስማት ሳያስፈልግ የትራፊክ ሪፖርት እንዲቀርብ ባሳሰቡት መሠረት ማስረጃውን በማስቀረብ መዝኖ ጉዳቱ የደረሰው በአንገፍ ጥፋት መሆኑ ስለተረጋገጠ የአመልካች ኃላፊነት በንግድ ሕጉ ቁጥር 599 መሠረት የሚወድቅ ስለሆነ ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት በቤታቸው የሠራተኛ ወጪ የሚያስከትልባቸው በመሆኑና ወደሥራ ሲሄዱ የሚያስፈልገውን የትራንስፖርት ወጪ በቀሪ ዕድሜያቸው ጊዜ በማስላት የጉዳት ካሣ ብር 228,000.00፣ የሕክምና ወጪ ብር 90,770.00፣ የምግብ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 ለተጠሪ እንዲከፍልና መድን ድርጅት ከሚከፍለው ብር 40,000.00 ውጭ ያለውን ካሣ አመልካች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ይግባኝ እና የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዘዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የሥር ፍርድ ቤት በ21/12/2012 ዓ/ም ተጨማሪ ማስረጃው ሊያያዝ አይገባም በማለት ብይን ከሰጠ በኋላ ብይኑን በራሱ ሽሮ የትራፊክ ሪፖርቱን በመቀበል መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ከተመለሰ በኋላ አዲስና ተጨማሪ ማስረጃ ሊቀበል አይገባም፡፡ ቋሚ የአካል ጉዳቱ 28% ሆኖ እያለ በ100% ጉዳት ካሣው መሰላቱ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ተመልክቶ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው መመሪያ መሰረት መወሰን አለመወሰኑን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ የሠጡት መልስ ግራቀኛችን የሠው ማስረጃ አናሰማም በትራፊክ ሪፖርት መሠረት ይወሰን በማለት ባሳሰብነው መሠረት ማስረጃው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቀርቦ ተመዛዝኖ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ ለተያዘው ጭብጥ አስፈላጊ ማስረጃ ተቀብሎ ካሣውን በርትዕ አመዛዝኖ ተገቢ ነው ተብሎ ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራኙን ክርክር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የአመልካች ሚኒባስ መኪና በሆነ ተሳፍረን በምንጓዝበት ጊዜ ከቆመ ተሽከርካሪ ጋር በመጋጨቱ በቀኝ እግሬ የታፋ አጥንት እና በግራ እግሬ ከጉልበት በታች አጥንት ስብራት በመድረሱ 28% ቋሚ አካል ጉዳት ደርሶብኛል፡፡ የጉዳት ካሣ ብር 406,230.00፣ የሕክምና ወጪ ብር

90,770.00፣ የአልሚ ምግብ ወጪ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 በድምሩ ብር 500,00.00 አመልካች እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ በንግድ ሕጉ መሠረት በውል ስትገዛ ነው ጉዳቱ የደረሰው፣ የቀረበው የጉዳት መጠን የተጋነነ በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ ቀደም ሲል እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በመዝገብ ቁጥር 180599 ሚያዚያ 29 ቀን 2012 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ ጉዳዩ በንግድ ሕጉ እንዲገዛ እና አንገዥ ጥፋት ያለበት መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ተመርመሮ እንዲወሰን ለሥር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡ የተመለሰለት ፍርድ ቤት ግራቀኙ ማስረጃዎቻቸውን ለማሰማት ባለመፈለጋቸውና የአንገዡ ጥፋት መኖር አለመኖር በትራፊክ ሪፖርት ተመስርቶ እንዲወሰን ማስረጃው እንዲቀርብ ባሳሰቡት መሠረት ማስረጃውን አስቀርቦ አንገዡ ጥፋት ያለበት ስለሆነ የአመልካች ኃላፊነት የሚወሰነው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 599 መሠረት ነው ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የሥር ፍርድ ቤት በ21/12/2012 ዓ/ም ተጨማሪ ማስረጃው ሊያያዝ አይገባም በማለት ብይን ከሰጠ በኋላ ብይኑን በራሱ ሽሮ የትራፊክ ሪፖርቱን በመቀበል መወሰኑ እና ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ከተመለሰ በኋላ አዲስና ተጨማሪ ማስረጃ መቀበሉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የመለሰው አንገዡ ጥፋት ያለበት መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ እንዲወሰን ሲሆን የተመሰረተው የፍሬ ነገርን ጭብጥ ያካተተ በመሆኑ ጉዳዩ በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባው ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዘረዘሯቸውን ማስረጃ ማሰማት እንዳልፈለጉና የፍሬ ነገር ጭብጡ በትራፊክ ሪፖርት መሠረት እንዲወሰን ማስረጃው እንዲቀርብ እንዲታዘዝ ያመለከቱ ስለመሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ፍርድ ቤት የማስረጃው መቅረብ አምኖበት ከአሶሳ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ማስረጃው እንዲያቀርብ ማዘዙም ጉዳዩ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 መሠረት መመራቱን ያመላክታል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 መሰረት ተከራካሪዎች ካቀረቧቸው የሠው ሆነ የሠነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆነ ማስረጃ ፍርድ ቤቱ የማስቀረብ ስልጣን እና ኃላፊነት እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ ሕጉ ኮመን ሎው እና ኮንቲኔንታል ሎው የሕግ ሥርዓት የሚከተሉ ሀገሮችን አጣምሮ የያዘ እና ከኮመን ሎው የህግ ሥርዓት ከሚከተሉ ሀገሮች በተለየ ለዳኛው ጉዳዩንና ግራቀኙ የሚያቀርቡትን ማስረጃ ከማዳመጥ ያለፈ ተግባር እንደሰጠው ያሳያል፡፡ ድንጋጌው እውነትን የመፈለግ ዓላማ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ እንዳለው የሚያሳይ እና ዓላማው እንዲሳካ የማድረግም ኃላፊነት የዳኛውም እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ወደሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩ የተመለሰው በፍሬ ነገር ጭብጥ ተመስርቶ ከመሆኑ አኳያ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ከተመለሰለት በኋላ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግና ፍትሐዊነትን ሊያሳካ በሚችል መልኩ ማስረጃውን እንዲቀርብ ከማድረግ ሕጉ የመከልከል ሀሳብ አለው ሊባል አይችልም፡፡ ተጠሪ የሕክምና ማስረጃና የትራፊክ ሪፖርት በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርብላቸው ጠይቀው የሥር ፍርድ

ቤት በ21/12/2012 ዓ/ም የሕክምና ማስረጃ ሊያያዝ የማይገባው ስለመሆኑ ብይን የሠጠ ቢሆንም አሁን አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የትራፊክ ሪፖርት በተመለከተ የሠጠው ትዕዛዝ ባለመኖሩ በክርክሩ ሂደት ማስረጃውን አስቀርቦ መዝኖ መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የማስረጃ አቀባበል ሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘውም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ተሳፍረውበት የነበረው ሚኒባስ በፍጥነት ሲሽከረከር መንገዱን ለቆ ከቆመ ከባድ ሎቤድ ተሽከርካሪ ጋር መጋጨቱ የተረጋገጠ ነው በሚል በንግድ ሕጉ አንጽ 599 መሠረት ጉዳቱ የደረሰው በአንገፍ ጥፋት ስለመሆኑ ድምዳሜ ላይ መድረሱን ይሕ ሰበር ሰሚ ችሎትም የሚቀበለው ነው፡፡ ተጠሪ ዘለቄታዊ የአካል ጉዳቱ 28% መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ጉዳት ከደረሰባቸው በኋላም መደበኛ ሥራቸው የቀጠሉ በመሆኑ በቀጥታ የገቢ መቋረጥ ያላስከተለ ቢሆንም በተጠሪ እግር ላይ የደረሠው ጉዳት ዘላቂ በመሆኑ አሁን የሚሠሩትን የሥራ ዓይነት ማከናወን ቢችሉም እንኳን ለወደፊት ማንኛውንም ዓይነት የሥራ ተግባር ማከናወን ላይ እክል እንደሚሆንባቸውና አጠቃላይ የመሥራት አቅማቸውን እንደሚቀነስ ይገመታል፡፡ የጉዳት ካሣ ሲወሰን ግምት ውስጥ መግባት ከሚኖርበት ጉዳይ አንዱ በአጠቃላይ በተጎጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመሥራት ኃይል ቅነሳ /General utility/ እንደሆነ በሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 19338 አስገዳጅ ትርጉም የተሠጠበት ነው፡፡ በአጠቃላይ የመሥራት ኃይል መቀነሱ ለወደፊት የሚደርስ ጉዳት (future damage) እንደሚያስከትል የሚታወቅ ሲሆን ትክክለኛ ጉዳቱ ግን ለማወቅና ለመለየት ስለሚያስቸግር በፍ/ሕ/ቁ. 2102 እንደተመለከተው ጉዳት መድረሱ ተረጋግጦ ነገር ግን የጉዳት መጠኑን ማወቅ ካልተቻለ ካሣውን በርትዕ መወሰን ይችላል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በርትዕ ካሣውን ለማስላት ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት ከሚያጡት ገቢ አንጻር ሳይሆን ጉዳቱ ከሚያስከትለው ተጨማሪ ወጪ በመነሳት በቤታቸው የሠራተኛ ወጪ የሚያስከትልባቸው በመሆኑና ወደሥራ ሲሄዱ የሚያስፈልገውን የትራንስፖርት ወጪ በቀሪ ዕድሜያቸው ጊዜ በማስላት የጉዳት ካሣ ብር 228,000.00 መወሰኑ ተጠሪ ሙሉ ገቢያቸውን እንዳጡ አድርጎ እንዳሰላው ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ምክንያታዊ የሆኑ ጉዳዮችን በመያዝ ካሣውን በርትዕ መወሰኑ ሆነ የሕክምና ወጪ ብር 90,770.00፣ ለምግብ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 አመልካችና በሥር ፍርድ ቤት ለተሽከርካሪው የመድን ሽፋን የሠጠው ጣልቃ ገብ በየድርሻቸው እንዲከፍሉ ውሳኔ መስጠቱ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 11078 ጥር 20 ቀን 2013 ዓ/ም፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 11058 ጥር 05 ቀን 2013 ዓ/ም እና የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12050 ታህሳስ 08 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ